# ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት፤ ሶስቱ የስልጣኔ ማዕዘናት

**አሸናፊ መለሠ**

**03-25-15**

*“አንድ ዜጋ እንደምርጥ ዜጋ ሊታጠቃቸው የሚገቡ ሶስት መሰረታዊ ትጥቆች አሉ፤ እነሱም፡- ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ናቸው”*

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ከላይ በጉልህ ተጽፎ ያነበባችሁት የዋና ዳይሬክተሩ ንግግር ነው፡፡ ከጥቅምት 21 እስከ ጥር 1፣ 2007 ዓ/ም በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲሰጥ በነበረው የመንግስት ስትራቴጂዎችና ስልጠና ላይ ዋና ዳይሬክተሩ ይህንን ንግግር ሲናገሩ በወቅቱ የሰጠሁት ምላሽ በስምምነት ራስን ከመነቅነቅና ንግግሩን በማስታወሻ ደብተሬ ከመከተብ ያለፈ አልነበረም፡፡ ሆኖም ለሌላ ጉዳይ ያንን ማስታወሻ ስገላልጥና ስመለከተው ግን የንግግሩን ቁም ነገሮች አፍታትቶ መመልከት ለተሻለ ግንዛቤ ይረዳል ብዬ አሰብኩ፡፡

## ዕውቀት (knowledge)

“እውቀት በወጣትነትህ ጌጥ፣ በጉልምስናህ ጊዜ የገቢ ምንጭ፣ በእርጅናህ ጊዜ ደግሞ ምርኩዝህ ነው” የሚለን ታላቁ የፍልስፍና አባት አርስቶትል ዕውቀትን በሶስት ይከፋፍለዋል፡፡

የመጀመሪያው የዕውቀት ምድብ ቴክኒካል ዕውቀት ሲሆን የዚህን የእውቀት አይነትና ጥቅም ሲያብራራም “በአለም ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ አምራች የሆነው የሰው ልጅ ብቻ ነው፤ ይህንን ምርታማነት ደግሞ ከተፈጥሮ ስለማያገኝ ከቀደሙት አባቶቹ የሚያገኘው የቴክኒክ ዕውቀት ያስፈልገዋል” ይላል፡፡ ሁለተኛው የዕውቀት ምድብ ስነምግባራዊና ፖለቲካዊ እውቀት (ethical and political knowledge) እንደሆነ ገልፆ፣ ይህ የሰው ልጅ ህይወት በሞራል ህግጋት ሊገራ የሚገባው እንደሆነ ያስረዳል፡ ፡ ይህ ካልሆነ ግን የራስ ወዳድነትና የበላይነት ስሜቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ገንነው በመውጣት ማህበራዊ ቀውስን እንደሚፈጥሩ ያስረዳል፡፡ (ይህን ዕውነታ የተረዳው የሳይንሱ ሊቅ አልበርት አንስታይንም “እውቀት በጨመረ ቁጥር ራስ ወዳድነት (ego) ይቀንሳል፤ እውቀት በቀነሰ ቁጥር ደግሞ ራስ ወዳድነት ይጨምራል” ማለቱን ማስታወስ ተገቢ ነው) አርስቶትል ገለጻውን ሲቀጥል የሰው ልጅ ፖለቲካዊ እንስሳ (political animal) በመሆኑ ይህንኑ በብቃትና በብስለት ይከውን ዘንድ እነዚህ እውቀቶች እንደሚያስፈልጉት ይጠቅሳል፡፡ ሶስተኛው የዕውቀት አይነት ንድፈሃሳባዊ እውቀት (theoretical knowledge) ሲሆን በዚህ ስርም በአዕምሮ የሚደረስባቸውና የማይደረስባቸው ጉዳዮች ይጠቃለሉበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የዲበ አካል (metaphysics) የፍልስፍናና የሒሳብ ዕውቀቶች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ባለንበት የግሎባላይዘሽን አለም ዕውቀት በየአዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ውስጥ ለራሱ አካል ሰጥቶ (embedded) የሚታይ ግዙፍ አዕምሮአዊ ንብረት (intellectual asset) ከመሆኑም ባሻገር የሃገራትን ኢኮኖሚ እስከመሸከም የደረሰ ተፅዕኖ ያለው

ሃብት እንደሆነ የዕውቀት ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡ ከሌሎቹ ሃብቶች በተለየ የዕውቀት ሃብት ቢለገስ የማይቀንስ፣ ቢሰራበት የማይደበዝዝ፣ ውጤቱም ሁሌ አትራፊ እንደሆነ የሚያስረዱት ሊቃውንቱ ይህንን ሃብት በቅጡ ለማስተዳደርም የዕውቀት ማኔጅመንት (knowledge management (KM)) የተባለ የጥናት ዘርፍ እስከመመስረት ደርሰዋል፡፡

በመሆኑም እንደ ህንድና ቻይናን በመሳሰሉት ሃገራት ዕውቀትን ለሃገራቸው እድገትና ብልፅግና እንደዋነኛ ሃብት ከመቁጠርም ባለፈ ለምዕራባውያን በመሸጥና በአዳዲስ የፈጠራ ብቃቶቻቸው በመገዳደር በኢኮኖሚ ፉክክሩ ውስጥ ወሳኙን ቦታ ለመያዝ ችለዋል፡፡

## ክህሎት (skill)

"ክህሎት ከጥንካሬም ይልቃል" ይላሉ ፖላንዶች የክህሎትን ብርታት ሲያስገነዝቡ፡፡

ለመሆኑ ክህሎት ምንድን ነው?

የካምብሪጅ ዲክሽነሪ ክህሎትን "በልምምድ የምንቀዳጀውና አንድን ስራ ወይም ተግባር በጥሩ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችለን ብቃት ነው" በማለት ይተረጉመዋል፡፡

"ክህሎት ሶስት ባህርያትን በጥምረት የያዘ ግለሰባዊ ብቃት ነው" የሚሉን ደግሞ የለንደን ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስና የክህሎት ልማት ፕሮፌሰሩ ፍራንሴስ ግሪን ናቸው፡፡ ፕሮፌሰር ግሪን What is Skill? An Inter-Disciplinary Synthesis በሚለው ጥናታቸው ስለሶስቱ የክህሎት ባህርያትን እንዲህ አስቀምጠዋል

1. አምራችነት (productive) ሁሉም ክህሎት አንዳች እሴትን የማምረት ብቃት ሊኖረው ይገባል፤
2. ተወራራሽነት (expandable) ክህሎት ለአንድ ግለሰብ እንደመክሊት የተሰጠ ተሰጥኦ ሳይሆን በትምህርትና በልምምድ ማንኛውም ሰው ሊጨብጠው የሚችል ብቃት ነው፤
3. ማህበራዊነት (social) ያ ክህሎት በሰፊው ማህበረሰብ ዘንድ በጠቃሚነቱ ተቀባይነትን ያገኘ መሆን አለበት፡፡

እ.ኤ.አ በ2008 በተባበሩት መንግስታት የወጣው የአለም ህዝብ ቁጥር ትንበያ እንደሚያመለክተው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ካለው የህዝብ ቁጥር ውስጥ 43 ከመቶው ለስራ የደረሰ ነው፡፡ "ይህ ማለት ደግሞ…" ይላል አለማቀፉ የሰራተኞች ቢሮ በ2010 የወጣው ጥናት ላይ "ይህ ማለት ደግሞ በእነዚህ ሃገራት ሊኖር የሚችለውን የትምህርት የስልጠናና የክህሎት አያያዝ አስቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል" ይላል፡፡ ይህንን ሲያብራራም በመጀመርያ ደረጃ በእነዚህ ሃገራት የዕድገት መሰረት የሚሆነው ዋነኛ ሃይል አምራቹ ክፍል ይሆናል፤ ይህን ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል በትምህርትና ስልጠና ለምርታማነት ብቁ እንዲሆን በመግራት በኢኮኖሚው ውስጥ መሪውን እንዲጨብጥ ማድረግ ወሳኝ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ሰፊ የሰው ሃይል በስራ ፈጠራ እንዲበረታታ በማድረግም የግሉን ክፍለኢኮኖሚ ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰው ሃይል ስደቱን ለመቆጣጠርም ይኸው ስራ በአግባቡ ሊከናወን እንደሚገባ ይመክራል፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ከሰሞኑ ያወጣው መረጃ የሃገራችን የህዝብ ቁጥር ወደ 90 ሚልዮን ገደማ መድረሱን ይናገራል፡፡ ይህ ቁጥር ደግሞ የኢኮኖሚ እድገታችንን ይበልጥ ለማፍጠንም ሆነ ወደ ኋላ ለማስቀረት ምርጫው በእጃችን መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ማለት እስካሁን እንደታየውና ውጤቱም በግልፅ እንደሚያመለክተው በሚልየን የሚቆጠረውን ወጣት የሰው ሃይል ክህሎትን አስታጥቆ ወደስራ ፈጣሪነት እንዲሰማራ ማድረግ በተለይም ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፣ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እድገትና ለኢንዱስትሪያላይዘሽኑ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ታላቅ ይሆናል፡፡ ከዚህ የህዝብ ቁጥር ውስጥ 19 በመቶ የሆነው በከተሞች ውስጥ የሚኖር መሆኑ ደግሞ ኢንዱስትሪያላይዘሽኑ እውን እንዲሆን የሚሰጠው ዕድል ቀላል አይሆንም፡፡ ነገር ግን ይህን ታላቅ የሰው ሃይል በክህሎት አበልፅጎ ወደስራ ማስገባት ካልተቻለ ይኸው ለልማት ይሆነናል ያልነው ሃይል የጥፋት ሃይል ሆኖ በሰፊ የማህበራዊ ቀውስ ውስጥ እንደሚነክረን አስቀድሞ ማወቅ ያሻል፡፡

## አመለካከት (attitude)

“አንተ እስካልተለወጥክ ድረስ የሚለወጥ ምንም ነገር የለም፣ አንተ ስትለወጥ ደግሞ የማይለወጥ የለም” ይላሉ ነጮቹ ስለ አመለካከት ተፅዕኖ ግዙፍነት ሲገልፁ፡፡

Beyond Intent: Crossing the Threshold to Your Dreams የተባለው መፅሃፍ አመለካከትን ራስን ለመመልከትና ለመለ'ወጥ ያለ ፈቃደኝነትና ከሚያዩትና ከሚሰሙትም ባሻገር ያላዩትና ያልሰሙት ጉዳይ አይጠፋምና ለአዳዲስ ሃሳቦች ራስን ክፍት የማድረግ ብቃት እንደሆነ ይናገራል፡፡

ሮጀር ፍሪትዝ THE POWER OF A POSITIVE ATTITUDE በተሰኘ መጽሃፋቸው ይህንን “ራስን የመመልከት ብቃት ለመለወጥ የመጀመርያው እርምጃ” እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ራስን መመልከት እንደ አባባሉ ቀላል ያልሆነና ለምናየውና ለምንሰማው ነገር የምንሰጠው ምላሽና ድርጊቶቻችን ስለራሳችን የሚናገሩት ሽርፍራፊ ጉዳይ እንዳለ ጠቅሰው እነዚህን ትናንሽ የማንነታችን ሽርፍራፊዎች በመገጣጠም ስለራሳችን ያለንን ምስል ማግኘት እንደምንችል ይነግሩናል፡፡

እውቀታችን ምንም ያህል ቢቆለል፣ በላያችን ላይ የደራረብነው ዲግሪ ምን ያህል ስሙና ደረጃው ቢደረጅ ለሃገር እንዲፈይድ፣ ለሰው ልጆች ችግር መፍቻነት እንዲውል ካላደረግነው በላያችን የቆለልነው ሰርተፍኬት ጀርባችንን ከማጉበጥ የተለየ ስራን አይሰራም፡፡

ፊደል መቁጠር በአባቶቻችን አባባል “አይንን መግለጥ፣ ክፉን ከደግ፣ መጥፎን ከጥሩ መለየት መቻል” ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ዕውቀት በክህሎት በልፅጎ በአመለካከት ካልተገራ ዋጋ ቢስ መሆኑ አይቀርም፡፡

የአሜሪካኑ የቀድሞው ፕሬዝደንት አብርሃም ሊንከን ጥሩ ዜጋ “ሀገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት” ሊል እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ ይህም ሃገርን መለወጥ የዜጎች ተግባር እንጂ የማንም የቤት ስራ እንዳይደለ ለማሳሰብ ይመስላል፡፡

የአመለካከት ችግር የዘመናት ችግራችን ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሃገራችን እንደሃገር ለሺህ አመታት ፀንታ ብትኖርም የህልውናዋን ያህል ግን በስልጣኔ አልተራመደችም፡፡ ሶስት ሺህ አመት ሙሉ በበሬ ያረስነው ለአዳዲስ ሃሳቦች በራችንን ስለዘጋን ነው፤ ሶስት ሺህ አመት ሙሉ “ጋራ ሸንተረሩ”ን የዘፈንነው ለሺህ ዘመናት ሳይታረስ የኖረን ድንግል መሬት እያማተርን ነው፤ ከአንዴም ሶስትና አራት ጊዜ በድርቅና በርሃብ የተንገላታነው አራሽ ገበሬያችን ለአንድ አመት እንኳ የሚሆን ጥሪት ማኖር ስላልቻለ ነበር ……

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ “የሚሰሩ እጆች፣ የሚያስብ ጭንቅላት፣ የወጣት ሃይል ይዘን ስንዴ የምንለምንበት ሁኔታ መቆም አለበት” የሚለውን ታሪካዊ ንግግር የተናገሩት የሚሰሩ እጆችም ሆኑ የሚያስብ ጭንቅላት እንዲሁም ተዓምር ሊሰራ የሚችል የወጣት ሃይል በአመለካከት ካልተገሩ ውጤት እንደማይኖራቸው ለማሳሰብ ነው፡፡

እናም ሁላችንም በተሰማራንበት ሙያ ላይ የሚጠበቅብንን ውጤት ለማስመዝገብ ለጽሁፌ መነሻ የሆነውን ሃሳብ ያነሱት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ያነሷቸውን ሶስት ጉዳዮች፣ ማለትም፣ ከማይነጥፈው የሰው ልጅ እውቀት የድርሻችንንና ያቅማችንን ያህል በመውሰድ እውቀታችንን ተግባራዊ ለማድረግ በክህሎት በመግራትና ይህን በእውቀት የተደገፈ ክህሎት ለተገቢው ዓላማ ለማዋል የሚያስችለንን ጤናማ አስተሳሰብ በመያዝ ልንንቀሳቀስ ይገባል፡፡ ያኔ እጆቻችን በስራ ይጠመዳሉ፤ ጎተራዎቻችን በምርቶቻችን ይሞላሉ፤ አንገቶቻችንም በኩራት ቀና ይላሉ፡፡ ያኔ፣ የሌለ የመሰለን፣ ቢኖርም ለዝንተአለሙ የተከረቸመ የመሰለን የስልጣኔ በር ወለል ብሎ ይከፈታል፤ የተሸከምነው የድህነት ተራራም እንደ እንቧይ ካብ አቅም አጥቶ ይንኮታኮታል፡፡